# የወል ምናብ

ተሳታፊዎች የወል ባህል ገጸ ባህሪዎች እና ተረኮች እንዴት ንቃት ለመፍጥር እና ለተለያዩ ዓላማዎች ዘመቻ ለማካሄድ እንዴት ጥቅም ላይ እንደዋሉ ያስሳሉ። ተሳታፊዎች አንድ ንቃት ለመፍጥር እና ለእነርሱ አስፈላጊ የሆኑ ዓላማዎች ዘመቻ ለማካሄድ ሊጥጠቅሙ የሚችሉ የወል ባህል ገጸ ባህሪና እና ተረክ ይለያሉ።

# የወል ባህል እና አራማጅነት

## ክፍል አንድ

***ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው***

በሚወዷቸው መጽሐፎች ውስጥ ያሉ ምስሎች፣ ትምህርቶች፣ ወይም ከሚወዷቸው መጻሕፍት ውስጥ ከሚገኙ ገጸ ባህርያት፣ ከፊልሞች፣ ከቲቪ ትርዒቶች የሚቀዱ ምሳሌዎች ስለ አንድ ዓላማ ግንዛቤ ለመፍጠር በጣም ጥሩ ዘዴዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ብዙውን ጊዜ፣ የልብ ወለድ ገጸ ባሕርያት የሕይወት ተሞክሮዎች ሰዎች በእውኑ ዓለም ጉዳዮች ላይ ያላቸው አመለካከት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ።

ለምሳሌ፣ ሃሪ ፖተር በቤት-ኤልቮች ላይ የነበረው አመለካከት በሕጻናት ባርነት ወይም በፋብሪካ ውስጥ ስላለ መጥፎ የሥራ ከባቢ የበለጠ እንዲያስቡ ሊያደርግዎ ይችላል። የጀምስ ካሜሮን አቫታር ከተለቀቀ በኋላ፣ በአካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ትኩረት ተፈጥሮ ነበር። ተደናቂ ገጸ ባህርያት ሰፊ የባህሪ ለውጦች ላይ ተጽዕኖ የማሳደር አቅም አላቸው፣ ይኸም ማነቃቃት በዘመቻ ወቅት በጣም ጥቃሚ ያደርጋቸዋል።

ሰፊ ተቀባይነት ያለው ባህል ተጠቅሞ አንድ አላማ የሚመለከት ግንዛቤ የማሳደግ ጉዳይ ለማጠናከር፣ የፕሮጀክሽን ስክሪን ላይ ከእርስዎ / ተሳታፊዎች አካባቢያዊ / ዘናዊ አውድ ጋር የሚጣጣም የቅርብ ጊዜ ቪድዮ እንደ ምሳሌ ያሳዩ።

ከዩናይትድ ስቴትስ አውድ (በእንግሊዝኛ) የተወሰደ ምሳሌ ብናይ የሀሪ ፖተር ደጋፊዎች በሃሪ ፖተር ጥምረት አማካኝነት የህጻናት ባርትን መከላከል ችለዋል። ይህንን ቪድዮ ካዩ በኋላ፣ ይህንን ቪድዮ ለምን እንደመረጡት እና በዝነኛ ባህል አማካኝነት አንድን ጉዳይ የሚመለከት ግንዛቤ የማደግ ሁኔታ የሚያሳይ ጥሩ ምሳሌ የሚሆንበት ምክንያት ያብራሩ።

***ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው***

በሚቀጥለው ምድብ ሥራ፣ የወል ባህል ወይም ታሪክን በመጠቀም የራስዎን የማነቃቃት ዘመቻ ያዘጋጃሉ።

# ምድብ ሥራ

## ክፍል አንድ

### *ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው*

በክፍሉ ዙሪያ እየተዘዋወርን እያንዳንዱ ሰው የሚወዱትን ገጸ ባሕሪ ወይም ታሪክ ስም እንዲጠቅሱ እናደርጋለን።

### የክላስ መስተጋብር

ተሳታፊዎች ሁለት ወይም ሶስት የሚወዷቸውን ተወዳጅ ገጸ ባሕሪዎች ስም እንዲጠቅሱ ያድርጉ። ከዚያ በኋላ፣ ተመሳሳይ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች በ 3 በሶስት ያቧድኗቸው።

### *ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው*

እንደ ቡድን፣ ለእርስዎ አስፈላጊ የሆነን ጉዳይ ለማስተዋወቅ ሊጠቀሙበት የሚችሉት የአንድ ገጸ ባህሪ ወይም ታሪክ ይምረጡ።

እንደ ቡድን፣ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልሶች ጻፉ:-

1. የእርስዎ የወል ባህል ገጸ ባሕሪ ወይም ታሪክ ማነው?
2. ገጸ ባሕሪውን ወይም ታሪኩን በመጠቀም ሊሰሩበት ያሰቡት ጉዳይ ምንድነው?
3. የማንቃት ጥረትዎን በየትኛው ፊልም፣ የሙዚቃ ቅንብር፣ ወይም የምናብ ዓለም ላይ ይመሰርታሉ?
4. እርስዎ በመረጡት ጉዳይ ላይ ንቃትን ለመፍጠር እንዴት አንድ ሚዲያ (ለምሳሌ፣ ሙዚቃ፣ ካርቱን፣ ፖስተር፣ ወዘተ) በሚወዱት የወል ባህል ቅርጽ ላይ ሊያዘጋጁ ይችላሉ?
5. ይህን ሥራ እንዴት በመስመር ላይ ማጋራት እና ከፍተኛ ቁጥር ያለው ታዳሚ ዘንድ መድረስ ይችላሉ?

ይህ መማሪያ ነገር በ Berkman Klein Center for Internet &amp ላይ በወጣት እና ሚድያ የቀረበ ነው; ሃርቫርድ ዩኒቨርስቲ ሶሳይቲ በ Creative Commons Attribution-ShareAlike 4.0 International ፈቃድ ስር። ወጣት እና ሚድያን እንደ ኦርጂናል ምንጭ እስከጠቀሱ እና ተጨማሪ ስራዎችን በተመሳሳይ ስምምነት መሰረት እስካከናወኑ ድረስ ከሱ የተወሰዱ ንግዳዊም ንግዳዊ ያልሆኑም ከሱ የተወሰዱ ነገሮች መጠቀም ይችላሉ። እነዚህን እና ተጨማሪ መማሪያ ነገሮችም Berkman Klein's Digital Literacy Resource Platform መስመር ላይ ይገኛሉ።